የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

(ግንቦት 12 -20/2016 ዓ.ም)
May 20-28/2024

**በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ**

1. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ እስያና መካከለኛው ምስራቅ በሚላክ የቡና ምርት ላይ በማጓጓዣ ክፍያ በአንድ ኪሎ ግራም እስከ 1 ነጥብ 50 ዶላር ቅናሽ ማድረጉን አስታወቀ፡፡

የአየር መንገዱ ካርጎና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ቡና ላኪዎችን ለማበረታታት እና የኢትዮጵያን ቡና በዓለም ለማስተዋወቅ የሚጫወተውን ሚና ማጠናከሩን ገልጿል፡፡

**Fanabc: ግንቦት 13፣ 2016**

በዚህም ወደ እስያ እና መካከለኛው ምስራቅ በሚልኩት የቡና ምርት ላይ በአንድ ኪሎ ግራም እስከ 1 ነጥብ 50 ዶላር ድረስ ቅናሽ ማድረጉን የአየር መንገዱ መረጃ አመላክቷል፡፡

https://www.fanabc.com/archives/246910

2. የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ለመጀመርያ ጊዜ ዋን ኤምአርኦ ለተሰኘ የግል ኩባንያ በግሉ ዘርፍ የመጀመሪያ የሆነውን የአውሮፕላን ጥገና ፈቃድ ሰጠ፡፡

ዋን ኤምአርኦ ኩባንያ ፈቃድ ያገኘበት የአውሮፕላን ጥገና (Maintenance, Repair and Operation) አገልግሎት፣ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ብቻ ሲሰጥ የነበረ ሲሆን፣ አየር መንገዱ ለግል የበረራ አየር መንገዶችም የጥገና አገልግሎት አቅራቢ ነው፡፡

**Reporter May 22, 2024**

የአውሮፕላን ጥገና አገልግሎቱ በአየር መንገዱ ራሱን የቻለ ክፍል ሲኖረው፣ ለሌሎች አየር መንገዶች የሞተር ጥገና፣ የአውሮፕላን አካል ክፍሎች ጥገናና የምህንድስና ማሻሻያዎች በማድረግ ይታወቃል፡፡

በሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአውሮፕላን ምዝገባና የበረራ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክተር አቶ ዮናስ ታደሰ፣ ኩባንያው የወሰደው ፈቃድ አውሮፕላኑ ካረፈ በኋላ መንገደኞች የሚሳፈሩበት ቦታ እንደቆመ አነስተኛ የጥገና ሥራዎች ላይ ሜንተናንስ ማከናወን የሚያስችል መሆኑን ለሪፖርተር ገልጸዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/129751/

3. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሰሞኑ አፈፃፀማቸውን ከገመገመላቸው መንግሥታዊ ተቋማት መካከል ግብርና ሚኒስቴር አንዱ ነው። በዚህም ላይ የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ ዶክተር የሚኒስቴሩንና የተጠሪ ተቋማትን የዘጠኝ ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርበዋል። ሚኒስትሩ በሪፖርታቸው ካቀረቧቸው ጉዳዮች መካከል የማዳበሪያ አቅርቦት፣ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት፣ የሌማት ትሩፋትና አረንጓዴ ዐሻራን የተመለከቱት ይገኙበታል።

**Ethiopian press agency May 20, 2024**

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 16 ነጥብ አምስት ሚሊየን ኩንታል ማዳበሪያ ጅቡቲ የደረሰ ሲሆን፤ ከዚህም ውስጥ 11 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታሉ ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ ተጓጉዟል። በመስኖ ስንዴ በምርት ዘመኑ ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር ለመሸፈን ታቅዶ ሁለት ነጥብ 97 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል።

https://press.et/?p=128177

4. 4. በአገሪቱ ከሚሰጠው ጠቅላላ የብድር መጠን በወጪና ገቢ ንግድ ላይ ለተሠማሩ ባለሀብቶች በከፍተኛ የብድር መጠን መቅረቡ፣ በአምራች ዘርፉ ላይ ጉዳት እያስከተለ መሆኑ ተገለጸ።

ይህ የተነገረው የኢንዱስትሪና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሲገመግም ነው።

**Reporter May 26, 2024**

ብሔራዊ ባንክ ከወር በፊት ይፋ አድርጎት የነበረው የፋይናንስ ስቴቢሊቲ ሪፖርት (Financial Stability Report) በአገሪቱ ያሉ ሁሉም ባንኮች፣ እስካለፈው ዓመት ሰኔ መጨረሻ ድረስ በሥራ ላይ ካዋሉት አጠቃላይ 1.9 ትሪሊዮን ብር ብድር ውስጥ፣ 23.5 በመቶውን የሰጡት ለአሥር ተበዳሪዎች መሆኑን ማስታወቁ አይዘነጋም።

https://www.ethiopianreporter.com/129852/

5. **5የወጪ ንግድ ክፍተቶችን ለመቅረፍ አዲስ ፕሮጀክት ለመቅረጽ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ፕሮዲዩሰር ኤክስፖርተርስ አሶሴሽን**

የአውሮፓ ኅብረት አዲስ መሥፈርት ከተተገበረ ችግር ውስጥ ይገባሉ ተብለው ከተጠቀሱ ዘርፎች ውስጥ አንዱ የሆርቲካልቸር ዘርፍ ሲሆን አዲስ የወጣውን የአውሮፓ ኅብረት መሥፈርት ሊያሟላ ካልቻለ ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለው የውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ እንደሚችል እስከመግለጽ ደርሷል፡፡

የኢትዮጵያን ምርቶች ከሚቀበሉ አገሮች በተከታታይ የሚወጡ የተለያዩ መሥፈርቶችን አላሟሉም የተባሉ የኢትዮጵያ ምርቶች ገዥ አገሮች ከደረሱ በኋላ እንዲመለሱ የተደረጉበት አጋጣሚዎች መፈጠራቸው ደግሞ ጉዳዩን የበለጠ አሳሳቢ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

**Reporter May 22, 2024**

ይህንን የወጪ ንግድ ማነቆ የሆነ ጉዳይ ዘላቂ መፍትሔ እንዲኖረውና ወደፊትም ሳይጠበቅ የሚመጡ የአገሮች አዳዲስ መሥፈርቶችን በቶሎ አውቆ የተጠየቀውን መሥፈርት ለማሟላት መፍትሔ ይሆናሉ ተብለው ከሚታሰቡ ዕርምጃዎች መካከል አምራችና ላኪዎችን አቅም ማሳደግ ለሚጠየቁት መሥፈርቶች በቶሎ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አሠራር መዘርጋት በቀዳሚነት የሚቀመጥ ሆኗል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/129817/**

6. ማራቶን ሞተር ኢንጂነሪንግ በመጪው ዓመት መጨረሻ ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ የተመረቱ ተሽከርካሪዎችን፣ ለገበያ ለማቅረብ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ፡፡

**Reporter May 26, 2024**

በተሽከርካሪዎች ንግድ በ2001 ዓ.ም. ሥራ የጀመረው ማራቶን ሞተር ኢንጂነሪንግ ከተቋቋመ በኋላ ለአራት ዓመታት ያህል በዚህ ሥራ ተሰማርቶ የቆየ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፣ የተለያዩ የሐንዳይ ተሽከርካሪዎችን በ2011 ዓ.ም. በአገር ውስጥ መገጣጠም መጀመሩ ይታወሳል፡፡

7. **2ኛው የዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኤግዚቢሽንና ሲምፖዚየም በአዲስ አበባ ይካሄዳል**

'ቢግ 5 ኮንስትራክት ኢትዮጵያ' ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኤግዚቢሽንና ሲምፖዚየም ለሁለተኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ከግንቦት 22-24/2016 ዓ.ም እንደሚካሄድ ተገለጸ።

**ኢዜአ፡ ግንቦት 20/2016**

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ከአጋር አካላት ጋር በመሆን ያዘጋጁት ሲሆን ኤግዚቢሽንና ሲምፖዚየም በመጪው ሐሙስ በሚሊኒየም አዳራሽ ይከፈታል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_4501720

## *በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች*

**9. Safaricom's Ethiopian Venture Surpasses 9 Million Customers**

Safaricom Telecommunications Ethiopia Plc, a subsidiary of Kenya's Safaricom, has achieved a milestone in Ethiopia's telecommunications market as its customer base surpasses 9 million.

Ethiopian business review: **May 23, 2024**

The impressive customer acquisition took place within a span of nine months, from October 2022 to December 2023. Safaricom's Ethiopia unit successfully onboarded over 9 million customers during this period, demonstrating the strong demand for its voice, SMS, and mobile money services.

**https://ethiopianbusinessreview.net/safaricoms-ethiopian-venture-surpasses-9-million-customers/**

**10. Mastercard, Kifiya launch program to expand success to credit for MSMEs**

The Mastercard Foundation, in partnership with Kifiya Financial Technology (Kifiya), announces a scale-up program designed to unlock resources from banks, innovate new financial models and products, and transition the financial sector to enable access to uncollateralized financial credit products for MSMEs.

**Capital Ethiopia:May 27, 2024**

According to the statement sent to Capital, a budget of USD 100 million is committed to the program.

The Sustainable Access to Finance to Enable Entrepreneurship (SAFEE) program incorporates learnings from Michu, a successful large-scale pilot by the Cooperative Bank of Oromia, Kifiya, and the Mastercard Foundation.

https://www.capitalethiopia.com/2024/05/27/mastercard-kifiya-launch-program-to-expand-success-to-credit-for-msmes/

11.

**11. Brics bank mulls funding for non-member States projects**

A multilateral infrastructural projects financier owned by the Brics countries is mulling over funding projects in countries outside the bloc's 11 members, unlocking additional finance for infrastructure upgrades in African nations like Kenya

**THE EAST AFRICAN: MAY 28 2024**

The New Development Bank (NDB), which is owned by the Brazil-Russia-India-China-South Africa (Brics) intergovernmental organisation, may soon be sending money to finance projects across the region, even as it lobbies for more African countries, including Kenya, to join the bloc.

**https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/brics-bank-mulls-funding-for-non-member-states-projects-4638588**

**12.**